የኢትዮጵያ፤የውዪዪትና መፍትሔ መድረክ (ኢውመመ)
**9900 Greenbelt RD. E#343 -** Lanham**, MD 20706 – Tel: 1-202-641-5517**

ነሐሴ, 2008 ዓ.ም

የኢትዮጵያውያን የውይይትና መፍትሄ መድረክ

EDF-Ethiopian dialogue Forum

## ወቅታዊ መግለጫ

የኢትዮጵያውያን የውይይትና መፍትሄ መድረክ በተለይ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚታየዉ የፓለቲካ ሁኔታ ያሳሰባቸው ምሁራኖች ፣ የፓለቲካ መሪዎች አክቲቪስቶችና አገር ወዳዶች በቅርቡ የመሰረቱት ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት ይዞት ከተነሳው አላማዎች አንደኛዉ ኢትዮጵያ ሃገራችን ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ላይ የምርምር ስራዎችን በመስራት አማራጭ መፍትሄዎችን ማቅረብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሃገሪቱ ውስጥ የሚታየዉ ሕዝባዊ የፓለቲካ ተቃውሞና ያለመረጋጋት ሁኔታ ወደ ከፋ ደረጃ ሳይደርስ ብሄራዊ ውይይት እና እርቅ ወርዶ ሃገሪቱ ፈጥና ወደ ዴሞክራሲ ጎዳና እንድትገባ ማድረግ ነው።

ከዚህ አንፃር እኛ የዚህ ድርጅት አባላት በተለይ ካለፉት በርካታ ወራት ጊዜ ጀምሮ በሃገራችን የሚታየውን መጠነ ስፊ ህዝባዊ ተቃዉሞዎችን እና በሕዝብ ላይ የሚካሄደውን ግድያ እያየን በንቃት እየተከታተልን እንገኛለን። ኦሮምያ ውስጥ ህዝባዊ እምቢተኝነት በተከታታይ እየተካሄደ ነው። በቅርቡ በአማራዉ ክልል በጎንደር ውስጥ የተጀመረው ህዝባዊ እምቢተኝነት ወደ ባህርዳርና ደብረ ማርቆስና ወደ ሌሎች የአማራ ክልል ክፍሎች ተዛምቷል። በጋምቤላና በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ ያለመረጋጋት እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያውያን በያሉበት ተበድለናል ብለው ተቃውሚቸውን በሰልፍ ሲገልፁ የኢትዮጵያ መንግስት ህወሓት/ኢህአዴግ ፈጣን ምላሽ ጥይት መሆኑ እጅግ አሳስቦናል። ለዜጎች የመብት ጥያቄ ጥይትና እስር አንዳችም መፍትሄ ሊሆን አይችልም። መንግስት የህዝቡን ጥያቄ በሃይል ለመገደብ ሲሞክር ከትናንቱ ዛሬ ተቃውሞው ጨምሯል። ሃገሪቱንም ወደ ከፋ ችግር እየወሰዳት ነው። በመሆኑም እኛ የዚህ ድርጅት መስራች አባላት የኢህአዴግ መንግስት፣

1. ሰላማዊ ሰልፈኞችን መግደል ማሰር ማንገላታቱን እንዲያቆም እንጠይቃለ፤ ግድያዎችን እናወግዛለን። በተለይ በኦሮምያና በአማራ ክልሎች የሚደረገው የስለላ፤ የማሰር፤ የመግደል እና የማሰደድ ሥራ በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።

2. የዜጎችን ህገ መንግስታዊና የሰባዓዊ መብት እንዲያከብር እንጠይቃለን።

3. የሰባዓዊ መብታቸዉን ለማስከበር ሲታገሉ የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞችና ጋዜጠኞች

ሁሉ ባስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

4. ሃገሪቱ ወደከፋ ችግር ውስጥ እንዳትወድቅ መንግስት ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር ባስቸኳይ ውይይት እና ድርድር እንዲከፍትና ሃግሪቱ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ እንድታመጣ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት እናሳስባለን።

5. በተጨማሪም በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር በኢትዮጵያ ውስጥ በአማራና ኦሮምያ ስለተፈፀመው የሰብአዊ መብት አፈናንና የንጹህ ኢትዮጵያዊያን ግድያን በሚመለከት ታዛቢዎችን ለመላክ አቅዶ የኢትዮጵያን መንግስት ቢጠይቅም የኢትዮጵያ መንግስት ፈቃደኛ አልሆነም። እኛ የኢውመመ አባላት ይህንን ምላሽ በፅኑ እያወገዝን በአስቸኳይ የኢትዮጵያ መንግስት ኮሚሽኑ ስራውን ስኬታማ እንዲያደርግ መንግሥት እንዲፈቅድ በጥብቅ እናሳስባለን።

6. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ሕብረትና የኢትዮጵያ ወዳጅ ሃገራት በተለይም የተባበረችው አሜሪካና ብሪታኒያ አገሪቱ ወደ ሰላማዊ የሽግግር ስርአት እንድትገባና ህዝብ የመረጠው መንግስት ስልጣኑን እንዲይዝ የበኩላቸዉን አስተዋፅኦ በማድረግ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንዲቆሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

7. በዚህ አጋጣሚ ድርጅታችን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንደቆመ በአክብሮት እንገልጻለን።

ሰላም እድገትና ብልፅግና ለኢትዮጵያ ሃገራችን

የኢውመመ-EDF- መስራች አባላት


## የኢትዮጵያ የውዪዪትና መፍትሔ መድረክ

The Ethiopian Dialogue Forum (EDF)
9900 Greenbelt RD. E#343 Lanham, MD 20706
Tel. +1-202-641-5517